

# በቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ውስጥ የልጅዎን ዝንባሌ መደገፍ

AMHARIC

በቅድመ ልጅነት ጊዜ ትምህርት ውስጥ አዎንታዊ የሆነ አጀማመር አስፈላጊ ነው። እርስዎ እና ቤተሰብዎ ቅቡልነት፣ ደህንነት እና ድጋፍ እንዲሰማዎት አስፈላጊ ነው። የአገልግሎቱ የመጀመሪያ ቀናት ስለ ልጆችዎ ሌላ ልጆችን ማወቅ እና ከመምህራኖቻቸው፣ አስተማሪዎቻቸው እና ሌላ የቅድመ ልጅነት ባለሞያዎች ጋር እምነት የሚጣልበት ግንኙነት ስለመጀመር ናቸው።

በቪክቶሪያ ያሉ የቅድመ ትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች የሚመሩት በቪክቶሪያ የቅድመ አመታት ትምህርት እና ልማት ማዕቀፍ (Victorian Early Years Learning and Development Framework (VEYLDF)) ነው። ይህ ማዕቀፍ የልጆች 'ማንነት እና ቤተሰባቸው ብሎም የባህል ታሪኮች ትምህርታቸውን እና እድገታቸውን እንደሚቀርፁ ለአስተማሪዎች ያሳውቃል። ልጆች ቅቡልነት የሚሰማቸው እና በደንብ የሚማሩት ባለሞያዎች ልዩ ማንነታቸው ሲያከብሩ እና ለዝያ ልዩ ማንነታቸው እውቅና ሲሰጡት ነው'(VEYLDF, 2016, ገጽ. 12)። ይህ ግንዛቤ አስተማሪዎች እርስዎን እና ልጅዎን በዝንባሌያቸው ወቅት እና ለአዲሱ የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎት በሚያቋቁሙበት ጊዜ ለመደገፍ የሚወስዱትን ዘዴ ያጠናክራል።

የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች በአስተማሪዎች እና ቤተሰቦች መካከል ያለውን የትብብር ሽርክና ጥራት ላለው ፕሮግራም እንደ መሰረት ያዩታል። ከመጀመሪያው ጀምሮ በአክብሮት የተሞሉ ግንኙነቶች ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት ጠንካራ አመላካች ናቸው። አስተማሪዎች ሞቅ ያሉ እና እንግዳ ተቀባይ እንዲሆኑ እንዲሁም የቤተሰብ ቋንቋዎ(ችዎ)ን መጠቀምዎን እንደሚያበረታቱ እንደሆኑ መጠበቅ ይችላሉ።

አገልግሎቶቹ በሚገባ የተረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ እና ጥያቄ የመጠየቅ እድል እና ለእስርስዎ በጣም ምቹ በሆነ ቋንቋ ተጨማሪ መረጃ እንዲፈልጉ ለማድረግ በስልክ በሚሰጠው የአስተርጓሚ አገልግሎት ከእርስዎ ጋር መገናኘትን ሊደግፉ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ የቤተሰብዎን ቋንቋ የሚናገር የድጋፍ ሰራተኛ ልጆችዎ በአገልግሎቱ ላይ አባልነት እስኪሰማቸው እና ግንኙነቶችን እስከሚያዳበሩ ድረስ ለአጭር ጊዜ ለማገዝ ሊገኝ ይችላል።

ጥራት ያለው የቅድመ ልጅነት ትምህርት ቤተሰቦችን እንደ ‘በልጆች ትምህርት እና መዳበር ላይ ቀዳሚ ተጽእኖ አድራጊ’ አድርጎ እውቅና ይሰጣል (VEYLDF, 2016, ገጽ. 9)። በቀዳሚ አመታት ፕሮግራሞች ላይ አስተማሪዎች ለቤተሰብ ግብአት እና ተሳትፎ ዋጋ ይሰጣሉ እንዲሁም ይፈልጋሉ። ይህ የአስተማሪዎቹን ተግባር ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን ልጆች በትምህርት እና እንክብካቤ አካባቢዎች እና የትምህርት ውጤቶችን በሚጨምሩ የቤት አካባቢዎች ባሉ ሰዎች መካከል እምነትን፣ ደህንነት እና ግንኙነትን እንዲያዳብሩ ጭምር ይረዳል። እንዲሁም ቤተሰቦች በአገልግሎቱ ላይ እንዲሳተፉ እና በመጀመሪያ ክፍለጊዜዎች ላይ እንዲገኙ ይበረታታሉ። ይህ ልጆችዎ ደህነነት እንዲሰማቸው እና ለእርስዎ ልጆችዎ በአገልግሎቱ ላይ ከእርስዎ ተለይተው በሚቆዩበት ጊዜ ምን እደሚፈጠር እንዲገነዘቡ ይረዳል።

የእርስዎ የቅድመ ልጀነት አገልግሎት እርስዎ እና ልጅዎ ከአገልግሎቶቹ ጋር በደንብ እንድትተዋወቁ ለመርዳት የዝንባሌ እቅድ ይኖረዋል። ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

- መደበኛ መገኘት ከመጀመሩ በፊት አገልግሎቱን ከልጅዎ ጋር መጎብኘት
- እርስዎ እና ልጅዎ ምቾት እንዲሰማችሁ ለማድረግ ከአጫጭር ክፍለ ጊዜዎች በመጀመር እስከ ረዣዝም ክፍለጊዜዎችን መገንባት።

የእርስዎ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ከእርስዎ ጋር ጊዜ ያሳልፋሉ እንዲሁም ስለእርስዎ እና ስለ ልጅዎ አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል። ይህ የልጅዎን ፍላጎቶችን በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤን ይሰጣቸዋል እና ለልጅዎ የመማር እድሎችን እና አዎንታዊ ውጤቶችን ከፍ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል።

የቅድመ ልጅነት አገልግሎቶች እዲያጋሯቸው ሊጠይቁዎት ለሚችሉት መረጃዎች ምሳሌዎች እነዚህ ናቸው፤

- ስለ ልጆቹ የጤና መረጃ – የክትባት መዝገቦች፣ የህክምና ፍላጎቶች፣ በሽታዎች ወይም አለርጂዎች።
- የዳይፐር ቅያሬ ምርጫዎች፣ የመጸዳጃ ምርጫዎች እና የቤት ውስጥ ልምዶች።
- ልጆች የሚበሉት ምግብ፣ የመመገቢያ ሰዓት ልማዶች/ ድግግሞሾች።
- የልጆቹ የእረፍት/ የእንቅልፍ ፍላጎቶች።
  - በአልጋ ላይ ይተኛሉ፣ በራሳቸው አልጋ ወይስ በጋራ ይተኛሉ?
  - ምን አይነት ሙዚቃዎች ምቾት ሊሰጧቸው ይችላሉ?
  - የሚወዱት መጽሃፍ፣ የተለየ አሻንጉሊት ወይም ብርድልብስ አላቸው?
  - በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚያርፉት/የሚተኙት ስንት ሰዓት ነው?
- ለቤተሰብዎ ምን አይነት በአላት እና ወጎች አስፈላጊ ናቸው?
- አስተማሪዎች ከእነሱ ጋር መጋራት የምትፈልጉትን ማንኛውንም ሌላ መረጃ በደስታ ይቀበላሉ።
- እንዲሁም እርስዎ አስተማሪዎች ስለልጅዎት እንዲያውቁ የሚፈልጉት እና ከልጅዎት ጋር እንዲገናኙ የሚረዱ መረጃዎች ይኖሩዎታል።

## ልጅዎን በቅድመ ልጅነት አገልግሎታቸው ውስጥ ሲገቡ የሚደገፉባቸው ሌሎች መንገዶች

- በአገልግሎቱ ላይ ከልጅዎ ጋር ጊዜ ያሳልፉ– የአገልግሎቱን የቀንተቀን ልማዶች ለልጅዎ አብራሩላቸው፣ አብራዋቸው ተጫወቱ፣ ታሪኮችን አንብቡ እንዲሁም ሙዚቃዎችን በራስዎት ቋንቋ ይዝፈኑ።
- ከሌሎች ልጆች ጋር እንዲግባቡ ደግፏቸው። ይህም ምናልባት በቀላሉ ከሌሎች አጠገብ እንዲቀመጡ በማበረታታት፣ ራሳችሁን ለሌሎች ልጆች በማስተዋወቅ፣ እንቅስቃሴዎች እና ጨዋታዎች ላይ በመቀላል ሊሆን ይችላል።
- ከልጅዎ እና ሌሎች ተመሳሳይ ቋንቋ ከሚያወሩ ሰዎች ጋር በመነጋገር ጊዜ ያሳልፉ።
- ከልጅዎ ጋር ስለሚያጋጥማቸው እና ስለሚሰማቸው ነገር ይነጋገሩ፤ ያረጋጓቸው እንዲሁም ያበረታቷቸው።
- ልጅዎ አስተማሪዎቻቸው ማን እንደሆኑ፣ ስማቸውን እና ማንኛውም አይነት እርዳታ ካስፈለጋቸው ወደ እነሱ መሄድ እንደሚችሉ እንደሚያዉቁ ያረጋግጡ። የመምህራኖቻቸውን ስም ከእርስዎ ጋር መጥራት እንዲለማመዱ እና እርዳታ መጠየቅን የሚለማመዱበትን እድል ስጧቸው።
- ሁልጊዜ ከመሄድዎ በፊት ልጅዎን ይሰናበቱ እናም በኋላ እንደሚመለሱ ያረጋግጡላቸው። ከመሄድዎ በፊት ልጅዎ ከአስተማሪ እና/ወይም ሌላ ልጅ ጋር እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገቡ በመርዳት እዲስማሙ ማድረግ ጥሩ ሃሳብ ነው።
- የሚያነሱት ምንም አይነት ጥያቄ ካለ እድል ለመስጠት እና እርስዎም ለሚኖራቸው ስጋት ምላሽ ለመስጠት ስለአገልግሎቱ አካባቢ እና ድግግሞሹ ከመገኘታቸው በፊት ባለው ማታ/ጠዋት ላይ ተወያዩ።
- የልጅዎ መምህራን እና አስተማሪዎች እርስዎን እና ልጅዎን በአገልግሎት ጊዜዎ ለመደገፍ እዚያ እንዳሉ ያስታውሱ።

**ዋቢዎች**

የትምህርት እና ስልጠና ክፍል፣ 2016። *የቪክቶሪያ የቅድመ አመታት የትምህርት እና ልማት ማዕቀፍ (Victorian Early Years Learning and Development Framework)*።